የሰ/መ/ቁ. 220133

ቀን ፡- ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ናፊሳ ዱቄት ፋብሪካ

ተጠሪ ፡- ቄስ ሰለሞን ዓለማየሁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ፤ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በነበረን የሥራ ግንኙነት የፋብሪካውን የምርት ውጤት እያጓጓዝኩ በተለያየ ቦታ ለመሸጥ እና የድካም ዋጋ ሊከፈለኝ ተስማምተን ከ2005 እስከ 2009 ዓ/ም ድረስ ምርቱን እየሸጥኩ ገንዘቡን ለአመልካች ገቢ አድርጊያለሁ፡፡ አመልካች የድካም ዋጋዬን ለመክፈል እምቢተኛ በመሆኑ አመልካች የእርቅ ሽማግሌዎች መርጦ በእኛ መካከል ያለውን ያለመግባባት ከተመለከቱ በኋላ ብር 706,788.00 እንዲከፍለኝ አስታርቀውናል፡፡ በእርቅ የተስማማነውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን አመልካች እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው መልስ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የእርቅ ውል ስላልሆነ ልከሰስ አይገባም፣ ተጠሪ ጋር የቀረብንን ገንዘብ በሽምግልና ጠየቅን እንጂ ከተጠሪ ጋር ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም ያደረግነው እርቅ ውል የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ቀደም ሲል አመልካች በመዝገብ ቁጥር 260606 በተጠሪ ላይ ገንዘብ እንዲከፈለው ክስ ባቀረበበት ፋይል ተጠሪም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው ግራቀኙ ጉዳያቸውን ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም በተደረገ እርቅ የጨረሱ በመሆኑ በእርቁ መሠረት አልተፈጸመልኝም የሚል ወገን ክስ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ሆኖ ከእርቅ ውጭ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውሳኔ የተሰጠበት እና እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ በመዝገብ ቁጥር 188170 ላይ የጸና ውሳኔ በመሆኑ ጉዳያቸው በእርቅ ያጠናቀቁ መሆኑን የቀደመው ውሳኔ ያመላክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች የእርቅ ውል የለም በሚል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ሊመረመር የሚገባው ጭብጥ በእርቅ ውሉ መሠረት መፈጸም አለመፈጸሙ ሲሆን አመልካች ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም በተደረገው እርቅ መሠረት ፈጽሚያለሁ የሚል ክርክር የለውም፡፡ ስለሆነም በዕርቅ ውሉ መሠረት ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን ገንዘብ ብር 706,788.00 ከሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በቀደመው ክርክር ለተጠሪ አልተወሰነለትም፣ አዲስ ክስ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ አጣርቶ መወሰን ሲገባው የቀደመውን ውሳኔ ጠቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የእርቅ ውል የለም በማለት ተከራክረናል፤ አመልካች ባልፈረመበት ረቂቅ ውል ሊገደድና ሊከፍል አይገባም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ተጠሪ ቀደም ሲል በነበራቸው ክርክር ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ ነው በማለት ተከራክረው ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተዘግቶ እያለ ጉዳዩን መሠረት በማድረግ ክስ አቅርበው ያስወሰኑበት አግባብነትን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የሠጡት መልስ በቀደመው ክርክር ጉዳዩ ላይ በሽማግሌዎች አማካኝነት እርቅ ያደረግን ስለመሆኑ ተረጋግጦ ተወስኗል፡፡ አመልካች ስለእርቅ ውሉ ፎርም ያቀረበው ክርክር በሥር ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፡፡ የተሠጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮው ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙ ክርክር፣ የሰበር አጣሪው ችሎት የያዘውን ጭብጥ፤ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በነበረን የሥራ ግንኙነት የፋብሪካውን የምርት ውጤት እያንጓዝኩ በተለያየ ቦታ ለመሸጥ እና የድካም ዋጋ ሊከፈለኝ ተስማምተን ከ2005 እስከ 2009 ዓ/ም ድረስ ምርቱን እየሸጥኩ ገንዘቡን ለአመልካች ገቢ ላደረግሁበት ሥራ ክፍያውን በለማስማማታችን አመልካች የእርቅ ሽማግሌዎች መርጦ በእኛ መካከል ያለውን ያለመግባባት

ከተመለከቱ በኋላ ብር 706,788.00 እንዲከፍለኝ አስታርቀውናል፤ በእርቅ የተስማማነውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን አመልካች እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የእርቅ ውል የለም፣ ከተጠሪ ጋር የእርቅ ውል ያላደረግሁ ስለሆነ ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል። የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን መርምረው ቀደም ሲል አመልካች ገንዘብ እንዲከፈለው ባቀረበው ክስ ተጠሪም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው ግራቀኙ ጉዳያቸውን ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም በተደረገ እርቅ የጨረሱ በመሆኑ በእርቁ መሠረት አልተፈጸመልኝም የሚል ወገን ክስ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ሆኖ ከእርቅ ውጭ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተወሰነ መሆኑን በመጥቀስ የእርቅ ውል መኖሩ አከራካሪ አይደለም። አመልካች ደግሞ በእርቅ ውሉ መሠረት አልፈጸመም በማለት በውሉ የተመለከተውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነዋል።

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ። መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር። ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ። በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ።

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ

ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራቀኙ መካከል የሥራ ግንኙነት የነበረ መሆኑ አልተካደም፣ የተጠሪ ክስ የተመሰረተውም በነበራቸው የስራ ግንኙነት ምክንያት አለመግባባት ተከስቶ ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም በተደረገ የእርቅ ውል አመልካች ብር 706,788.00 ሊከፈል ስለተስማማን ገንዘቡን ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች የእርቅ ውል አልተደረገም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች አሁን ከቀረበው ክስ በፊት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 260606 ባቀረበው ክስ ተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍለው ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው ባደረጉት ክርክር ጉዳዩ በእርቅ አልቋል የሚል ክርክር ከግራቀኙ በመቅረቡ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሆነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 167753 ላይ መርምረው ሕዳር 02 ቀን 2010 ዓ/ም የተደረገ የእርቅ ውል መኖሩን አመልካችም አምኗል፣ በእርቅ ውል መሠረት ለተጠሪ የሚከፈል ገንዘብ ብር 706,788.00 ስለመሆኑ በይዘቱ መመልከቱን አረጋግጠው በእርቅ የጨረሱት ጉዳይ ላይ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፤ በእርቅ ውሉ መሠረት ያልተፈጸመለት ወገን ይህን ጠሶቀ አዲስ ከማቅረብ ውሳኔው የማይገደው ስለመሆኑ አመላክተው ወስነዋል፡፡ ምንም እንኳን ቀደም ሲል ያደረጉት ክርክር ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢሆንም አመልካች እርቅ ውል መኖሩን ማመኑ በውሳኔው ተመላክቷል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በውሉ መሠረት አልተፈጸመልኝም በሚል ላቀረቡት ክስ አመልካች ውሉን ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ በአመልካች የእምነት ቃል መሠረት እርቅ መኖሩ ተረጋግጦ የተወሰነውን መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ እርቅ መደረጉ አከራካሪ አይደለም፣ በእርቁ መሠረት አመልካች ያልፈጸመ ስለሆነ ብር 706,788.00 ከወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 326165 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 211137 ታህሳስ 08 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*